# አክሊሉና ዝንጀሮ



29-30ኛው ሳምንት
1ኛ ክፍል
መጽሐፍ 13

# አክሊሉና ዝንጀሮ

መጽሐፍ 13 | 1ኛ ክፍል | 29-30ኛው ሳምንት



ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በፓክት ኢትዮጵያ (Pact Ethiopia) እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children) እና በትምህርት ሚኒስቴር ተሻሽሎ ታተመ::

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*



አክሊሉ ልብሱን በሳሙና ያጥባል።



ዝንጀሮ ከዛፍ ላይ ሆኖ ቁልቁል ይመለከታል።



አክሊሉ ውሃ አለቀበት።

ውሃ ሊቀዳ ወደ ቡዋንቡዋው

ሄደ።



ዝንጀሮ ከዛፍ ላይ ዘሎ ወረደ:: በሁለት እግሩ ቆመ:: ግራና ቀኝ ተመለከተ::



ዝንጀሮው የአክሊሉን ልብስ ይዞበት ከዛፉ ላይ ወጣ። አክሊሉ ሲመለስ ልብሱን አጣው።



አክሊሉ ዙሪያውን ቃኘ
ምንም ነገር የለም።
ወደላይ አንጋጠጠ፤ ዝንጀሮው
ልብሱን ይዞ ቁልቁል ሲያይ
ተመለከተው፤ አክሊሉ ልብሱን
ለማስመለስ ዘዴ ፈለገ።



አክሊሉ አንድ ልብስ አንስቶ ወደፊት ወረወረ። ዝንጀሮም እንደእሱ የያዘውን ልብስ ቁልቁል ወረወረ። አክሊሉ ሮጦ ልብሱን ወሰደ።

USAID
ከአሜሪካን ህዝብ